## ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ". ዘፍ14፡22

# ኪዳን አለኝ

**ሰኞ - August 12,2024**

**የንባብ ክፍል - የማርቆስ ወንጌል ከም1- ም3**

ይህ የማርቆስ ወንጌል መግቢያ ክፍል ስለመጥምቁ ዮሐንስ ማንነት እና አገልግሎቱን ከብሉይ ኪዳን አንጻር፣ የኢየሱስን ውኃ ጥምቀት እና በምድረበዳ መፈተን ያስረዳል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እና እግዚአብሔር ያቀደው የማዳን እቅድ እየተከናወነ መምጣቱን ያስታውቃል። ስለዚህም ሰዎችን የእግዚአብሔር መንግሥት ስለቀረበች ንስሐ እንዲገቡ እና በወንጌል እንዲያምኑ ጥሪ ያቀርባል።

ማር. 1፥14-15፤ "ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና፦ ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሐ ግቡ፥ በወንጌልም እመኑ፥ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።"

## ከምንባቡ የተወሰዱ የጸሎት ርዕሶች

1. ከፊት ይልቅ እግዚአብሔር መንግሥት ወደእኛ መቅረቡን እንደረዳ እንጸልያለን።
2. ለተቀበልነው የመንግሥቱ ወንጌል የሚመጥን ህይወት ባላሳየንበት፣ እንደሚገባ ባልተመላለስንበት መንገድ ሁሉ ንስሐ እንገባለን። 3. በወንጌል ማመን አንድ ጊዜ አድርገን የምፈጽመው ሳይሆን በተደረዳነው መጠን ከእምነት ወደ እምነት የምንሸጋገርበት እንደሆነ ከሮሜ 1፥17 ይናገራል። "ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።" ስለዚህ በማመን እያደግን እንድንሄድ እንጸልያለን።

**ማክሰኞ - August 13,2024**

**የንባብ ክፍል - የማርቆስ ወንጌል ከም4- ም7**

የምሳሌዎች ቁልፍ ትምህርቶች (4፡1-20)

ማርቆስ ባለው ክፍል (ም.1-3) እንዳሳየን የጌታን ማንነት እና መልእክቱን የሚቃወሙ ነበሩ። ኢየሱስ መሲሑ ሆኖ መምጣቱን እና አገልግሎቱን የሚቃወሙት ለምን እንደሆነ በምሳሌው ማስረዳት ጀመረ። የኢየሱስ ነጥብ ለአገልግሎቱ መቃወም የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እቅድ አካል ነው። የአፈር ምሳሌው የሚያብራራ የእግዚአብሔር እቅድ ግለሰቦች ለቃሉ በሚሰጡት ምላሽ አመለካከታቸውን እንዲፈጽሙ መፍቀድ ነው (4፡1–9፣ 13–21)። በሌላ አነጋገር፣ የክርስቶስን አገልግሎት መቃወም የእግዚአብሔር ሉዓላዊ እቅድ አካል ነው። አስተውለው ለሚሰሙ፥ ለሚቀበሉ እና ለሚታዘዙ ህይወትን እንዲያፈራላቸው በምሳሌው ያስረዳል፤

## ከምንባቡ የተወሰዱ የጸሎት ርዕሶች

1. ም.8፥20 ላይ እንደተገለጸው ዘወትር በመልካም ልብ ቃሉን ሰምተን እንድንቀበለው፣ ፍሬም እንዲበዛልን እንጸልያለን።
2. ማርቆስ ወንጌልን ስንማር ጌታ የገለጠልንን እውነቶች እያሰብን ንስሃ በገባንበት፣ እምነት ባገኘንበት፣ ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት

በተቀበልነባቸው ነገሮች ሁሉ ጸንተን እንድንቆም እና ወደፊት መራመድ እንዲሆንልን እንጸልያለን።

**ረቡዕ August 14,2024**

**የንባብ ክፍል - የማርቆስ ወንጌል ከም8- ም10**

ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ማን መሆኑን እና የአገልግሎቱን አላማ አለመረዳታቸው በተደጋጋሚ በማርቆስ ወንጌል ተገልጿል። ይህ ከክቡር ኃይሉ እና አገልግሎቱ ብሩህነት ጋር በእጅጉ ይቃረናል። ማርቆስ የኢየሱስ ደቀመዝሙር የሆነ ሁሉ የኢየሱስን ማንነት እና አገልግሎቱን እንዲያስተውል አጥብቆ ያስገነዝባል። ኢየሱስን ለመምሰል እና እርሱ እንደተመላለሰ ለመመላለስ ይህ መገለጥ እጅጉን ያስፈልጋል።

ማር. 8፥27-29 "ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስ ቂሣርያ ወዳሉ መንደሮች ወጡ በመንገድም፦ ሰዎች እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። እነርሱም፦ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ፡ ብለው ነገሩት። እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። ጴጥሮስም፦ አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰለት።"

## <u>ከምንባቡ የተወሰዱ የጸሎት ርዕሶች</u>

1. የእግዚአብሔር ልጅ እና መሲህ የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን በማወቅ እና ሥራውን በመረዳት እያደግን እንድንኖር እንጸልያለን።
2. ደቀመዛሙርቱ "አንተ ክርስቶስ ነህ" ሲሉት የራሳቸው የሆነ ስ ዕል ነበራቸው። የሚሞት እና የሚሰቃይ ሳይሆን ከቅን አገዛዝ ነጻ የሚያወጣቸው፣ መንግሥትን የሚመልስላቸው መሲህ ነበር የሚጠብቁት። ከተሳሳተ አመለካከት እንድንድን እጸለይን፣ ሌላ ኢየሱስ በመስበክ የሚሰራውን አጋንንትን እና ትምህርታቸውን እንቃወማለን።

**ሐሙስ - August 15,2024**

**የንባብ ክፍል - የማርቆስ ወንጌል ከም11- ም13**

ማር. 11፥20-26 "ማለዳም ሲያልፉ በለሲቱን ከሥርዋ ደርቃ አዩአት። ጴጥሮስም ትዝ ብሎት፦ መምህር ሆይ፥ እነሆ፥ የረገምሃት በለስ ደርቃለች፡ አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ በእግዚአብሔር እመኑ። እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ፦ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር፡ ቢል ይሆንለታል። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል። ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት። እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።"

ከምዕራፍ 11 ጀምሮ ያለው ታሪክ ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደኢየሩሳሌም ሲገባ እና በዚያ ከመከራው በፊት የሰጠውን ትምህርት እና አገልግሎት ነው። በመንገድ ሳሉ የተፈጸመው የበለሲቷ ታሪክ ትልቅ ምሳሌነት አለው። ፍሬ አልባነቷ የእሥራኤልን የተበላሸውን አምልኮ እና ፍሬቢስነት የሚያመለክት ሲሆን መድረቋ ድግሞ በእስራኤል ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ትንቢት ነው።

## <u>ከምንባቡ የተወሰዱ የጸሎት ርዕሶች</u>

1. ጤናማ መንፈሳዊ የግል ህይወት፣ ጤናማ ቤተክርስቲያን ሲኖረን አንዱ ምልክቱ በመንፈሳዊ ፍሬዎች ማደግ ነው። ይህ እንዲበዛልን እናጸልያለን።
2. ለዚህ ደግሞ ጸሎት ትልቅ ሥፍራ ያለው ሲሆን የጸሎት ህይወታችን የሚያስፈልጉት ሁለት ነገሮችን ጌታ ጠቅሷል፦ እምነት እና ይቅር መባባል። እነዚህ ነገሮች በየእለቱ የምንለማመዳቸው እና የምንጨምርባቸው እንዲሆኑልን እንጸልያለን።

**ዐርብ - August 16,2024**
**የንባብ ክፍል - የማርቆስ ወንጌል ከም14- ም16**

ማር. 15፥33-39 "ስድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ፥ እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ። በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም፡ አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው። በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው፦ እነሆ፥ ኤልያስን ይጠራል፡ አሉ። አንዱም ሮጦ ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞላ በመቃም አድርጎ፦ ተዉ፤ ኤልያስ ሊያወርደው ይመጣ እንደ ሆነ እንይ፡ እያለ አጠጣው። ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ። የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ። በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ፦ ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ፡ አለ።"
የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተፈጠረ ድንገተኛ አልነበረም። በቅዱሳት መጻሕፍት የተተነበየ መለኮታዊ ዕቅድ ነበር። ኢሳይያስ 53:10 እንደሚለው "እግዚአብሔርም ክፉኛ ያደቅቀው ዘንድ ፈቅዶ ነበር"። እናም በአንድ ጊዜ አሳዛኝ እና አስደናቂ የሆነ ክስተት የታየበት እና ሲጠብቁ የነበሩት ብዙ ትንቢቶች ፍጻሜ የተገለጠበት ምስጢር ነበር። በመጽሐፍ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ የሆኑትን ነገሮች ልብ እናድርግ።

## ከምንባቡ የተወሰዱ የጸሎት ርዕሶች

1. መስቀሉ ለክርስትና እምነታችን ዋና እና መካከለኛ ነው፣ ያለ መስቀሉ እውነተኛ የወንጌል መልእክት የለንም። 1 ቆሮ.15፥1-4 ይህ እውነት በእኛ ኑሮ በህብረታችን መካከል በየእለቱ የምንለማመደው እንዲሆንልን እንጸልያለን። መስቀሉን ከሚሸፍኑብን ነገሮች ሁሉ እንድንጠበቅ እንጸልያለን።
2. ይህ የክርስቶስ መስቀል፦ የኃጢአትን አስከፊነት እና የእግዚአብሔር ቁጣ ማሳይ፣ ኢየሱስ ምትክ ሆኖ የእኛን ቦታ መውሰዱን፣ የኢየሱስ የበደላችን ስርየት ማስገኛ እና የእግዚአብሔርን ቁጣ ማብረጃ መሆኑን መግለጫ፣ ከአብ ጋር ወደ ነበርንበት ህብረት ለመመለስ መታረቂያ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር ለእኛ አለውን ፍቅር ያስረዳበት ማስረጃ መሆኑን ይበልጥ ልብ እንድንል አይኖቻችን እንዲከፈቱልን እንጸልያለ።




**ረቡዕ እኩለ ቀን 11፡30 Am-1፡00 PM ያለው ሳምንታዊ ጸሎት ይኖረናል**


የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች ቤተክርስቲያን

Ethiopian Evangelical Believers Church

3001 Saturn Rd. Garland TX 75041

214.703.0100 | www.Eebcdallas.org